# የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር "በንግድ ሕጉ መሠረት በባለአክሲዮን ውክልና የመሳተፍ መብት አድማስ ወይም "Exercising Proxy Right under the Commercial Code" በሚል ርዕስ ያዘጋጀው ዓውደ ጥናት ቃለ-ጉባዔ

- **የስብሰባው ቦታ፡-** ዋቤ ሸበሌ ሆቴል
- **የስብሰባው ቀን፡-** ጥቅምት 26 ቀን 2009 ዓ.ም. ከጠዋቱ 3፡00 እስከ ከቀኑ 7፡00 ሠዓት
- **ጽሑፍ አቅራቢ፡-** አቶ ኃይሉ ቡራዩ/ጠበቃና የሕግ አማካሪ/
- **አወያይ፡-** አቶ ማርሻል ፍቅረማርቆስ/የቀድሞ ቡና ኢንተርናሽናል ባንክ የቦርድ ሊቀመንበርና የሕግ አማካሪና ጠበቃ/
- **በስብሰባው ላይ የተገኙ፡-** የማኅበሩ አባላት፣ የሕግ አማካሪዎች፣ ጠበቆች፣ የግልና የመንግሥት ባንኮች ተወካዮችና የፍ/ቤት ተወካዮች

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት አቶ ታምራት ኪዳነማርያም የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክታቸውን ካስተላለፉ በኋላ ማኅበሩ በዕለቱ ያሰናዳው ትምህርታዊ ውይይት "Exercising Proxy Right under the Commercial Code" ወይም በአማርኛው **"በንግድ ሕጉ መሠረት በባለአክሲዮን ውክልና የመሳተፍ መብት አድማስ"**ን በሚመለከት ሲሆን ጥናታዊ ጽሑፉም የሕግ አማካሪና ጠበቃ በሆኑት በአቶ ኃይሉ ቡራዩ የሚቀርብ ሲሆን መድረኩን በመምራት ውይይቱን የሚያካሂዱልን የቀድሞ ቡና ኢንተርናሽናል ባንክ የቦርድ ሊቀመንበርና የሕግ አማካሪና ጠበቃ የሆኑት አቶ ማርሻል ፍቅረማርቆስ ናቸው፡፡

ማኅበራችን ከያዛቸው ተከታታይ የትምህርት እቅድ መርሃግብሮች መካካል ይህ ትምህርታዊ ውይይት አንዱ ሲሆን የንግድ ሕግ ኮሚቴ በማኅበሩ ውስጥ ያዋቀርን ሲሆን ወደፊት በንግድ ሕጉ ዙሪያ ሰፊ ሥራ የምንሰራ መሆኑን እየገለፅኩ ይህ ውይይት የተዘጋጀው ግን በተከታታይ ትምህርት ኮሚቴ በኩል መሆኑን ለመግለፅ እወዳለሁ በማለት በዚህ መድረክ ላይ እንዲገኙ የተጋበዙ ተሳታፊ አካላትን ለመዘርዘር ሙከራ የተደረገ ሲሆን ከተለያዩ የግል እና የመንግሥት ባንኮች፣ ከብሔራዊ ባንክ፣ ከፌደራል ፍ/ቤቶች፣ ከአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች፣ ከጠቅላይ ዐ/ሕግ፣ ከንግድ ሚኒስቴር፣ ከኢንቨስትመንት ባለሥልጣን ወዘተ ይገኙበታል ብለዋል፡፡ በመጨረሻም ውይይቱ እጅግ ፍሬያማ እና መልካም እንዲሆን እመኛለሁ በማለት መድረኩን ለአወያዩ አስረክቧል፡፡

## አቶ ማርሻል ፍቅረማርቆስ - አወያይ (የሕግ አማካሪና ጠበቃ የቀድሞ ቡና ኢንተርናሽናል ባንክ የቦርድ ሊቀመንበር)

አወያዩይህ ትምህርታዊ ውይይት በመዘጋጀቱ የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበርን አመስግነው በሀገራችን ካላው የኢኮኖሚ እድገት እና የኩባንያዎች መበራከት ጋር ተያይዞ አንገብጋቢ እየሆነ የመጣው የኩባንያ እና የአክሲዮን ማኅበራት ሕግ መሆኑ የሚታወቅ መሆኑን አውስተው የንግድ ሕጉ በንጉስ ኃይለሥላሴ ማለትምበ1952 ፀድቆ ሥራ ላይ የዋለ ቢሆንም የንግድ ሕጉን በሰፊው መጠቀም የተጀመረው ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከአክሲዮን ማህበራት አቅም ማደግና ቁጥር መብዛት ጋር ተያይዞ እንደመጣ አስቀምጠዋል፡፡ አክለውም አንድ ባለአክሲዮን በተለያዩ ግላዊ ምክንያቶች በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ላይ ለመሳተፍ የማይችል እንደሆነ እንደራሴውን በመሾም በጉባኤው ወይም በሌላ አስፈላጊ ጉዳዮች ላይ ተሳታፊ ሊሆን ይችላል፡፡ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ላይ ለመሳተፍ የሚሰጠው ውክልና በሕጉና በተግባር የሚታዩ ክፍተቶች መኖራቸውን፣ በፍትሐብሔር ሕጉም ቢሆን የተለያዩ የሕግ ክርክርን የሚያስነሱ የእንደራሴነት ጥያቄዎች መኖራቸውን እና በተመሳሳይ የንግድ ሕጉ ላይም ይህ ዓይነት የሕግ ጥያቄዎች ያሉ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ የአቶ ኃይሉ ቡራዩ ጥናታዊ ፅሁፍም እነዚህን የሕግና የተግባር ጥያቄዎችን ማዕከል ያደረገ መሆኑን ጽሑፍ አቅራቢው አቶ ኃይሉ በሕግ የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ዲግሪ ያላቸውና ከወረዳ እና አውራጃ አስተዳዳሪነት ጅምሮ በተለያዩ የአስተዳደር እርከን በመንግሥት እና በግል መ/ቤቶች ያገለገሉ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ የሕግ አማካሪና ጠበቃ በመሆን እየሠሩ እንደሚገኙ ሰፋ ያለ ግላዊ የሙያ ታሪካቸውን ለታዳሚው ከገለጹ በኋላ በጽሑፍ አቅራቢነት በመሰየማቸው ምሥጋና በማቅረብ በቀጥታ ጽሑፋቸውን እንዲያቀርቡ በመጋበዝ መድረኩን ለአቶ ኃይሉ ቡራዩ አስረክበዋል፡፡

## አቶ ኃይሉ ቡራዩ

የጽሑፉ አርዕስትበንግድ ሕጉ መሠረት በባለአክሲዮን ውክልና የመሳተፍመብት አድማስን በሚመለከት መሆኑን ገልፀው ይህ ርዕሰ-ጉዳይ ከንግድ ሕጉ ክፍል ውስጥ አንገብጋቢና ወቅታዊ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ በዚህ ትምህርታዊ ውይይት ላይ በዋናነት የምንመለከተው ባለአክሲዮኖች በጠቅላላ ጉባዔ ላይ መገኘት በማይችሉበት ጊዜ ወኪል (proxy) የመሰየም ጉዳይ ጋር የተያያዙ በሕግ እና በተግባር የሚታዩ ክፍተቶችን ለመዳሰስ ሲሆን ባንኮችንና የመድን ተቋማትን በተመለከተ ብሔራዊ ባንክ የሚቆጣጠራቸው በመሆኑ በተወሰነ መልኩም ቢሆን ወጥነት ያለው አሰራር የሚከተሉ ይሁኑ እንጂ ሙሉ በሙሉ ከችግር ነፃ ናቸው ማለት አይቻልም፡፡ በሌሎች አክሲዮን ማኅበራት ደግሞ ችግሩ የተባባሰ መሆኑ እሙን ነው፡፡ አክሲዮን ማህበራቱ ወጥ የሆነ ፎርም

የላቸውም፡፡ በዛሬው ዕለት የሚደረገው ትምህርታዊ ውይይት ውጤት በሦስት መልኩ ጥቅም ላይ የሚውል ሲሆን የመጀመሪው በሕጉ ዙሪያ የተሳታፊዎችን እውቀት ለማነቃቃትና ለማስታወስ የሚረዳ መሆኑ፤ ሁለተኛው ለጥናታዊ ጽሑፉ ሕትመት እንደማዳበሪያነት የሚያገለግል መሆኑ እና በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ በቅርቡ ለሚሻሻለው የንግድ ሕግ እንደወሳኝ ግብዓት ሊጠቅም ይችላል፡፡

ፕሮክሲ የሚለው ቃል ከ1182 የንግድ ሕጉ አንቀፆች መካከል 5 ጊዜ ብቻ የተጠቀሰ መሆኑን እነዚህም አንቀፅ 398፣ 402፣ 403፣ 421፣ እና 358 መሆናቸውን ጠቅሰው ምንም እንኳን አንቀጾቹ ውስን ቢሆንም በይዘትና በአከራካሪነታቸው ግን ሰፊ ናቸው ብለዋል፡፡ በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ በሚደረግ ጊዜ ባለአክሲዮኑ በጉባዔው የመሳተፍ እና ሌሎች ብዛት ያላቸውመብቶችእንዳሉት የንግድ ሕጉ በአንቀፅ 345 እና 389 ላይ የተደነገገ ሲሆን የባለአክሲዮኖች መብት ከሚባሉት የትርፍ ድርሻ፣ ማኅበሩ ሲፈርስ ከተጣራው ኃብት ድርሻ፣ ድምጽ የመስጠትና የማግኘት መብት፣ የአክሲዮን ግዥ የቀደምትነት መብት፣ የማኅበሩን ውሳኔ የመቃወም መብት ወዘተ እንዳላቸው ያስቀምጣሉ፡፡

አንድ ባላክሲዮን የኩባያንው ጠቅላላ ጉባዔ በሚካሄድበት ጊዜ እራሱ በአካል እየተገኘ ቢሳተፍ ተመራጭ ቢሆንም ሰዎች በተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ወዘተ ምክንያቶች ላይገኙ እንደሚችሉ በመጥቀስ የንግድ ሕጉ በአንቀጽ 398 መሠረት ባለአክሲዮን በእንደራሴው ሊወከል እንደሚችል መደንገጉን አስታውሰዋል፡፡ስብሰባውን አባሉ በራሱ ወይም በወኪሉ ሊሳተፍ እንደሚችል ሕጉ በአንቀፅ 420 (2) በተጨማሪነት እንደሚከተለው ተመልክቷል፡፡

*<u>አንቀጽ 420 በጉባዔው ስለመግባት</u>*

*(2) በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ ተቃራኒ ውሳኔ ከሌለ በቀር ማንኛውም ባለአክሲዮን አንዱን ሦስተኛ ወገን ባለአክሲዮንም ባይሆን ለመወከል ይችላል፡፡*

ይሁን እንጂ የአንድ ኩባንያ የአስተዳዳሪ ምክር ቤት አባል (a member of board of directors) በምክር ቤት ስብሰባ ላይ መገኘት ካልቻለ እንደራሴ ሊሾም የሚችል ቢሆንም በእንደራሴነት ሊወከል የሚችለው ሰው ግን በዚሁ የምክር ቤት አባል በሆነ ሰው ብቻ እንደሆነና እንደራሴ መሆን የሚቻለው ለአንድ አባል ብቻ እንደሆነ የንግድ ሕጉ በአንቀፅ 358 (1) እና (2) በግልጽ የተመላከተና የምክር ቤት አባል የሆነ ሰው እንደ ባላክሲዮን ለሦስተኛ ወገን ውክልና ሊሰጥ እንደማይችል አስረድተዋል፡፡ የኩባንያ ምክር ቤት (board of directors) አባላት በእያንዳንዱ የኩባንያው የዕለት ተለት ሥራ ላይ የማይገቡ ይልቁንም የጠቅላላ ፖሊሲ ሥራ ለምሳሌ ወለድ በምን መልኩ ይሰጥ

ወዘተ የሚሉ ጉዳዮች ላይ የሚመክር መሆኑን አስረድተዋል፡፡ የአክሲዮን ማኅበር ምክር ቤት አባላት ለአንድ ሌላ አባል እንጂ ለሌላ ሦስተኛ ወገን የእንደራሴነት ሹመት የማይሰጥ መሆኑ ሕጋዊ ገድብ የተደረገበት ዋነኛ ምክንያት የኩባንያ ሚስጥር መጠበቅ ጋር የተያያዘ እና የቦርድ አባል ሲመረጥ በግላዊ ማንነቱ ላይ ከፍተኛ እምነት ስለሚጣልበት ጭምር እንደሆነ አብራርተዋል፡፡ ነገርግን ለጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ አንድ ባለአክሲዮን ለፕሮክሲ ውክልና ከሰጠ በኂላ እራሱ መጥቶ መሳተፍ የማይችል ሲሆን አንድ ወኪል ከብዙ ባላአክሲዮኖች ውክልና ወስዶ መስራት የሚችል መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ይሄ በበኩሉ አንድ ሰው የፈለገው ሰውበተለያየ ደረጃ እንዲመረጥ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

ፕሮክሲ ማለት ባለአክሲዮኑ ጠቅላላ ጉባዔ ሲደረግ መገኘት ባለመቻሉ ለሌላ ሰው ውክልና የሚሰጥበት ሁኔታ ሲሆን ሦስት ዋና ዋና ነገሮችን ለመወከል ወይም ለመግለፅ እንጠቀምበታለን፡፡ የመጀመሪያው ውክልናውን የወሰደው *እንደራሴ(ተወካዩ ሰው)* በራሱ ፕሮክሲ ሊባል ይችላል፡፡ ሁለተኛው ውክልናው የተሰጠበት *ፎርም ወይም ሰነድ* በራሱ ፕሮክሲ የሚባል ሲሆን የመጨረሻው ደግሞ በውክልናው የሚተላለፈው *ሥልጣን*በራሱ ፕሮክሲ ተብሎ ሊጠራ ይችላል በማለት አብራርተዋል፡፡

የፍትሓብሔር ሕጉ አንቀፅ 2179 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች በፕሮክሲ እና በባለአክሲዮኑ መካከል ያለውን የእንደራሴነት ግንኙነት የሚገዛ ሲሆን ፕሮክሲ ባለአክሲዮን በሆነ የተፈጥሮ ወይም ሕጋዊ ሰውነት በተሰጠው አካል የሚሰየም ነው፡፡ ፕሮክሲ እንደባለአክሲዮን በመሆን ተሳታፊ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ፕሮክሲው በወረቀት ድምፅ ከመስጠት ባለፈ በጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ በእለቱ በተያዘ አጀንዳ ላይ ለመናገር፣ ለመደገፍ ወይም ለመንቀፍ ይችላል ወይ?የሚለው ጥያቄ መሠረታዊ እንጂ ውይይት የሚሻ እንደሆነ ጠቁመው የተለያዩ ሀገራት ተሞክሮን ለመዳሰስ ጥረት የተደረገ ሲሆን ቀደም ብሎ በነበረው ጊዜ በህንድ እና በእንግሊዝ ሀገራት ፕሮክሲ በወረቀት ብቻ ድምፅ መስጠት ካልሆነ በቀር የመናገር መብትም ሆነ ሥልጣን እንደሌላቸው በመግለፅ የዚህን ምክንያት ሲያስረዱም ተወካይ ወካይን ተክቶ ለመናገር የወካዩን ስሜት፣ እይታ፣ አረዳድ እና ሥነልቦና ይዞ በራሱ አንደበት መግለፅ በፍፁም የማይችል በመሆኑ የሌሎችን ስሜት የሚጎዳ መመለስ የማይችል ጥፋት በንግግሩ ሊፈፅም ይችላል የሚል እምነት ስለነበራቸው እንደሆነ ነገርግን ይህ ግምት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ እና እየተለወጠ ከ1960ዎቹ ወዲህ ፕሮክሲ በወካይ እግር ገብቶ መናገር፣ መንቀፍና መደገፍ የሚቻልበት የሕግ ሥርዓት መፍጠራቸውን ገልፀዋል፡፡

በሀገራችን ያለውን ሁኔታ ስንመለከት ሕጋችን በዝርዝርና በግልፅ ያስቀመጠው ነገር የለም፡፡ በተግባር ያለውን ሁኔታ ስንገመግም ተወካዮች በወረቀት፣ በድምፅ፣ በምልክት (እጅ በማውጣት) እና/ወይም በጭብጨባ ድምፃቸው ይሰጣሉ፡፡ አንድ ኩባንያ የሚቋቋመው ትርፍ ለማግኘት መሆኑ የሚታመን መሆኑ፤ ተወካይ ደግሞ ለኩባንያው ወይም ለማኅበሩ የውጭ ሰው ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ያለው ተቆርቋሪነት የማይኖር ወይም አናሳ መሆኑ የኩባንያውን ጥቅም ሊጎዳ ይችላል በሚል ድምፅ የመስጠቱ ሥልጣን በወረቀት የተገደበ መሆን አለበት ሊባል ይችላል፡፡ ባለአክሲዮን የአክሲዮን ማኅበሩ አባል ለሆነ ወይም ለሌላ ሦስተኛ ወገን ውክልና መስተት እንደሚችል ቀደም ብለን ስንነጋገርበት የቆየን ሲሆን አንድ ፕሮክሲ ከተሰየመ በኋላ ግን አክሲዮን ማኅበሩ በጠቅላላ ጉባዔው ከተሳትፎ ሊያግደው እንደማይችል አስቀምጠዋል፡፡ የዚህ ምክንያትም ወኪሉ እንዳይሳተፍ ማድረግ የባለአክሲዮኑ መብትን እንደማገድ ስለሚታሰብ መሆኑንም አስረድተዋል፡፡

የአክሲዮን ማኅበራት ጠቅላላ ጉባዔ የሚደረግበት ሠዓት፣ ቦታ፣ አባል መገኘት የማይችል እንደሆነ ወኪል መሰየምየሚቻል መሆኑን የስብሰባ ጥሪ ማስታወቂያው የሚናገር ሲሆን ባለአክሲዮኑ ከአንድ በላይ አክሲዮን ያለው እንደሆነ ስንት ፕሮክሲዎችን ሊሰይም እንደሚችል አይናገርም፡፡ አንድ ባለአክሲዮን ያለው የአክሲዮን ብዛት ግምት ውስጥ ሳይገባ መወከል የሚችለው ፕሮክሲ አንድ ብቻ መሆኑን የንግድ ሕጉ በአንቀፅ 398 (1) ሥር የተመለከተ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

*__አንቀፅ 398 የባለአክሲዮኖች እንደራሴነት__*

(1) *አንድ ባለአክሲዮን ከአንድ እንደራሴ በቀር ለመሾም አይችልም፡፡ በጉባዔውም ላይ እንደራሴ አድርጎ ራሱ ድምፅ መስጠት አይችልም፡፡*

ይህ ማለት በቁጥር 100 የሚሆን አክሲዮን ያለው አባል 60ውን ለአንድ ፕሮክሲ ቀሪውን 40 ደግሞ ለሌላ ፕሮክሲ መስጠት አይችልም ማለት እንደሆነ በምሳሌ አስረድተዋል፡፡ በሀገራችን ድምፅ ከፋፍሎ መስጠት (cumulative voting) የተከለከለ ሲሆን በሌሎች ሀገራት ግን ድምጽን ከፋፍሎ የመስጠት ሁኔታ ገደብ አልተደረገበትም ብለዋል፡፡ ንግድ ሕጋችን በአንቀጽ 407 (1) ሥር እንደተመለከተው ለአንድ አክሲዮን አንድ ድምፅ መርህ ስለማካተቱም አብራርተዋል፡፡ ድምጽ እጅ በማውጣት ወይም ለዚሁ አገልግሎት በተዘጋጀ ፎርም ላይ ለውሳኔ የቀረበ ጉዳይን ድምፅ በመስጠት ወይም በመክልከል መደገፍ ወይም መቃወም ይቻላል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በቅርቡ ባወጣው መመሪያ በፋይናንስ ድርጅቶች ጠቅላላ ጉባዔ ሲደረግ ድምፅን በጭብጨባ የመስጠትን አካሄድ እንዲቆም ያደረገ ቢሆንም በተግባር ግን ይህ ሥርዓት ስለመቅረቱ እጠራጠራለሁ ብለዋል፡፡ ለምሳሌ የጠቅላላ ጉባዔ ፀሐፊ

ለመምረጥ ድምፅ እጅ በማውጣት የሚሰጥ ሲሆን የዚህ ዓይነት የድምፅ አሰጣጥ አካሄድ ብዙ አክሲዮን ያለውም ሰው ቢሆን እንኳ የሚቆጠረው በነብስወከፍ ደረጃ እንደሆነ አብራርተዋል፡፡ ነገር ግን በወረቀት በሚሰጥ የድምፅ ቆጠራ ሂደት ግን የአባሉ የአክሲዮን መጠን ግምት ውስጥ ያስገባ ነው ብለዋል፡፡ በወረቀት ድምፅ በሚሰጥበት ወቅት ፕሮክሲው ምርጫውን ማከናወን ያለበትወካዩ በሰጠው መመሪያ መሠረት መሆን አለበት፡፡ ነገርግን ፕሮክሲው ከተሰጠው መመሪያ ውጭ ድምፅ ሰጥቶ እንደሆነ ምን ይሆናል የሚል ጥያቄ አንስተዋል፡፡ የንግድ ሕጋችን ይህን የማይመልስ ሲሆን እንደ ህንድ እና እንግሊዝባሉ ሀገራት ፕሮክሲው ከወካዩ ፍላጎት እና አቅጣጫ ውጭ የሰጠው ድምፅ የፀና ሆኖ ለወካይ ግን ውክልናውን ለማንሳት በቂ ምክንት ይሆናል በማለት ገልፀዋል፡፡ ወካዮች አንድ አንድ ጊዜ ተሸዋሚ እንደራሴያቸውን ለመታዘብ ወደ ጉባዔው ይገባሉ፡፡ ይህ ማለት ግን ሁለት ጊዜ ድምፃቸውን ያስቆጥራሉ ማለት ግን አይደለም፡፡ በሌሎች ሀገራት የወካዩ በጉባዔው ላይ መገኘት ውክልናው እንደሌለ ወይም እንደተሻረ ግምት በመውሰድ ወካይ ድምጽ እንዲሰጥ ይደረጋል ብለዋል፡፡ በንግድ ሕጋችን አንቀፅ 398 (1) ስር እንደተመለከተው ወካይ እንደራሴ ከሾመ ድምፅ መስጠት አይችልም ብለዋል፡፡ በአንድ አንድ ሀገራት በወረቀት ድምፅ መስጠትን ውክልና በመስጠት የመናገሩን ሥልጣን ለራሳቸው አስቀርተው በጉባዔው ላይ ይገኛሉ፡፡

በሀገራችን ውክልና በሁለት መንገድ የሚሰጥ ሲሆን አንደኛው በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ፅ/ቤት ሲሆንሌላኛው ደግሞ ኩባንያው ወይም አክሲዮን ማኅበሩ በሚያዘጋጀው የውክልና ቅፅ ወይም ፎርም ይሆናል፡፡ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት የሚሰጥ ውክልና የቴምብር ቀረጥ እና የአገልግሎት ክፍያ የሚፈፀምበት ሲሆን ኩባንያ የሚያዘጋጀው ፎርም ግን ያለቴምበር ቀረጥ የሚስተናገድ ሲሆን ወካይ ፎርሙን በመሙላት ፕሮክሲው የወካይ እንደራሴ መሆኑን ያሳውቃል በማለት በሁለቱም አካል የሚሰጠው ፕሮክሲ ልዩ ውክልና እንደሆነ አስረድተው በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ የሚሰጠው ውክልና እስካልተሸረ ድረስ የፀና የሚሆን ሲሆን በኩባንያው ፎርም የሚሞላው ግን ለአንድ ጠቅላላ ጉባዔ ብቻ የሚያገለግል እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ ፕሮክሲ ጠቅላላ ጉባዔ ከመደረጉ ከ3 ቀን ወይም ከ72 ሠዓት በፊት ለአክሲዮን ማኅበሩ መቅረብ እንዳለበት የንግድ ሕጉ በአንቀፅ 402 ስር እንሚከተለው ተመላክቷል፡፡

> *<u>አንቀፅ 402፡- የእንደራሴነት ሥልጣን</u>*
>
> *የእንደራሴነት ሥልጣኖች ፎርም የሚቀመጡበትን ጊዜና ቦታውን የሚወስኑ አስተዳዳሪዎቹ ናቸው፤ ይህም ሲሆን የተባለው ጊዜ ጉባኤው ከሚሰበሰቡበት ከሦስት ቀን በፊት ለማለቅ አይችልም፡፡*

ጠቅላላው ጉባዔ ከመደረጉ ከሙሉ ሦስት ቀን በፊት ፕሮክሲ እንዲደርሳቸው የተፈለገበት ምክንያት ከውክልናው ጋር በተያያዘ ማጣራት የሚገባቸው ቁምነገሮችን ለማከናወኛ ጊዜ ነው፡፡ ለምሳሌ ፕሮክሲው በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 123 መሠረት የሲቪል መብቱ ተገድበው ከሆነ ወይም በአዋጅ ቁጥር 592/00 አንቀፅ 13 መሠረት በሕግ ከተሰጠው ከባለአክሲዮኖች ብዛት ያለው ወይም ከመጠን በላይ አክሲዮን በውክልና በመውሰድ ክንዱ ፈረጠመ ተፅዕኖ ፈጣሪ እንዳይሆን በዚህ 72 ሠዓት ውስጥ የምክር ቤቱ አባላት ወይም ቦርድ ኦፍ ዳይሬክተርስ ተገቢውን ማጣራት እንዲያደርጉ እድል ይፈጥርላቸዋል በማለት አብራርተዋል፡፡በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ የሚሰጠው ልዩ ውክልና በወካይ (principal) እስካልተሻረ ድረስ ፀንቶ የሚቆይ በመሆኑ እዚህ ላይ ሕጋዊነቱን ማረጋገጥ ብቻ በቂ ይሆናል፡፡ በአክሲዮን ማህበሩ የሚሰጥ ውክልና ፎርም ከምንም ዓይነት የቴምብር ቀረጥ ክፍያ ነፃ ሲሆን ከቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር 110/90 አንቀፅ 3 (11) ግን ቀረጥ መከፈል እንዳለበት የሚያስቀምጥ በመሆኑ የዚህን አሰራር ሕጋዊነት በጥያቄነት አንስተዋል፡፡

ከላይ የተመለከትነው የንግድ ሕጉ አንቀፅ 402 ሥር ፕሮክሲው ለኩባንው አስተዳደሪዎች ይቀርባል የሚል ሲሆን አስተዳዳሪዎች ማለት ደግሞ በንግድ ሕጉ አንቀፅ 347 መሠረት የምክር ቤት (ቦርድ) አባላት እንደሆኑ ያስቀምጣል በተግባር ግን ፕሮክሲው የሚቀርበው ለሥራ አስፈፃሚው ሲሆን የፕሮክሲውን ሕጋዊነትና ድምፅ መስጠት መቻል አለመቻሉን የሚያረጋግጡት ሌሎች አካላት (ለምሳሌ ሕግ ክፍል፣ ኦዲተር፣ ፋይናንስ ክፍል ወዘተ)ናቸው፡፡ በህትመትና በብሮድካስት ሚዲያው የሚሰራጩ የአክሲዮን ማህበራት የመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔም ሆነ ድንገተኛ ጉባዔ ጥሪዎች በሕጉ ላይ ከተቀመጡ ሁኔታዎች ወጣ ያሉ ናቸው፡፡

የፕሮክሲ ሥልጣን በጽሁፍ መሆን እንዳለበት የፍ/ብሔር ሕጉ በአንቀጽ 1725 (ሐ) ያስቀምጣል፡፡ በህግ ፊት የፀና ፕሮክሲ ከተሰጠ በኋላ ወካይ ለምክር ቤት (ለቦርድ) አባልነት ታጭቶ ቢመረጥ ተወካዩ ተገኝቶ እንደ ተመራጭ መቅረብ ይችላል ወይ የሚለው እንደ ጥያቄ ተነስቶ የነበረ ሲሆን ፕሮክሲ ወካይን ወክሎ ድምፅ መስጠት መቻሉ ግልፅ ሆኖ ድምፅ መቀበል ስለመቻሉ ግን በኢትዮጵያ ሕግም ሆነ የሌሎች ሀገራት ተሞክሮ ምላሽ የሚሰጥ አለመሆኑን አስረድተው አንድ ባለአክሲዮን ሲመረጥ የባለአክሲዮኑ ግላዊ እውቀትና ብቃት፣ ታማኝነት፣ ታታሪነት፣ ጤንነት፣ ማኀበራዊ ግንኙነት ወዘተ ላይ የተመሠረተ መሆኑ ይታመናል ስለሆነም ወካይ ለምርጫ ሲጠቆም ተወካይ አለሁ ብሎ ለመቅረብም ሆነ ለመመረጥ አይችልም ብለዋል፡፡

አክሲዮን እንደማንኛውም ዋጋ ያለው ንብረት ሊሸጥ፣ ሊለወጥ ወይንም በመያዣነት ሊያዝ ይችላል፡፡ አንድ ባላአክሲዮን ላለበት ዕዳ ወይም ኃላፊነት ያለውን አክሲዮን ለአበዳሪው ወይም ለሌላ ባለመብት

ሊያስይዝ የሚችል መሆኑን ገልፀው አንድ ባለአክሲዮን ከላይ በተጠቀሰው አኳኋን አክሲዮኑን ቢያስይዝ በአክሲዮን ማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ ለመሳተፍ የሚችለው ባለአክሲዮኑ ወይንስ አክሲዮኑን በመያዣነት የያዘው ሰው የሚለው አከራካሪ ጥያቄ እንደሆነ ጠቁመው ይበልጥ ደግሞ በዚህ ጭብጥ ላይ በፍ/ብሔር ሕጉ እና በንግድ ሕጉ መካከል ያለው ግልፅ ተቃርኖ ሁኔታውን ከባድ የሚያደርጉት ሲሆን የሁለቱም ሕጎች ድንጋጌዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

የፍትሓብሔር ሕጉ አንቀፅ 2870 እንደሚከተለው ይነበባል፡-

*አንቀፅ 2870፡- በመያዣ የተሰጡ አክሲዮኖች*

*አክሲዮኖች በመያዣ በተሰጡ ጊዜ በአክሲዮኔሮቹ ጉባዔ ላይ የሚቀመጠው አክሲዮኔሩ እራሱ ነው እንጂ አክሲዮን በመያዣ የተቀበለው ባለገንዘብ አይደለም፡፡*

የንግድ ሕጉ አንቀፅ329 እንደሚከተለው ይነበባል፡-

*አንቀፅ 329 መያዣ ወይም የአላባ መብት*

(1) *አንድ አክሲዮን በመያዣ ወይም በአላባ መብት የተሰጠ እንደሆነ ታቃራኒ ስምምነት ከሌለ በቀር በጉባዔዎች ድምፅ የመስጠት መብት አክሲዮኑን በመያዣ ለተቀበለው ወይም ለአላባ ጥቅም ተቀባዩ ነው፡፡*

በንግድ ሕጉ መሠረት ተቃራኒ ስምምነት ማለትም ባለአክሲዮኑ እራሱ በጉባዔ እንዲሳተፍ በግልፅ ስምምነት የሌለ እንደሆነ አክሲዮኑን ለዕዳ ዋስትና የያዘው ባለገንዘብ የሚሳተፍ መሆኑን ህጋዊ መብት ለባለገንዘቡ ያጎናፀፈ ሲሆን በአንፃሩ የፍትሐብሔር ሕጉ በበኩሉ በስብሰባው የመሳተፍ መብቱን ለባለአክሲዮኑ ያስቀራል ወይም ይሰጣል:: በዚህ ረገድ የፍትሓብሔር ሕጉና የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች እርስ በእርስ ይፃረራሉ፡፡

በተለያዩ ሀገራት ባለአክሲዮኖች በጉባዔዎች ላይ መገኘት ሳይችሉ ሲቀሩ ድምፅ በፖስታ አማካኝነት የሚሰጥ ቢሆንም ይህን አሠራር የሚደግፍ የሕግ ማዕቀፍ የለንም፡፡ ምንም እንኳን የአክሲዮን ማህበር አባላት ድምፃቸውን በፖስታ የመላክ ሁኔታን የሚነፈጉ ቢሆንም ኃላፊነታቸው በተወሰኑ ማኅበራት ላይ ግን ጉባዔ ሳይደረግ በሚሰጡ ውሳኔዎች ላይ አባላቱ ወይም ማንኛውም ማኅበርተኛ ድምፁን በጽሁፍ መስጠት እንደሚችል የንግድ ሕጉ አንቀፅ 533 ይደነግጋል ብለዋል፡፡ አሁን ካለው የቴክኖሎጂ እድገት ጋር ይህ ዓይነት አሠራር ለአክሲዮን ማህበራትም ተግባራዊ መደረግ እንዳለበት ገልፀዋል፡፡

በወረቀት በሚፈፀም ምርጫ እና እጅ በማውጣት የሚከናወን ምርጫ በቆጠራ የሚለያዩ ሲሆኑ መሠረታዊው ልዩነትም በወረቀት በሚደረግ ምርጫ እያንዳንዱ ባለአክሲዮን ማኅበርተኛ በኩባንያው ውስጥ ባለው የአክሲዮን ድርሻ መጠን የሚሰጠው ድምፅ የሚቆጠርለት ሲሆን ከጊዜ አንፃር እጅ በማውጣት የሚሰጥ ድምፅ የተሻለ ቀልጣፋ እና ውጤቱም ወዲያው የሚገለፅ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡ በሁለቱም የምርጫ መንገዶች መሳተፍ የሚቻለው በኩባንያው አባላት መዝገብ ስሙ ከተመዘገበ ብቻ መሆኑን ለመመዝገብ ደግሞ መስራች አባል መሆንን፣ ከኩባንያው ወይም ከሌላ ባለአክሲዮን አክሲዮን የገዛ መሆንን፣ በውርስ፣ በስጦታ ወይም በሌላ በማናቸውም ሕጋዊ አግባብ የአክሲዮን ባለቤትነተ የተላለፈለት ሰው መሆንን የሚጠይቅ እንደሆነ አብራርተዋል፡፡ በሀገራችን የአክሲዮን ባለቤትነት ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው የሚተላለፍበት መንገድ የመጀመሪያው በባለአክሲዮኖች መዝገብ ላይ ስመንብረቱ ስለመዛዋወሩመመዝገብ ሲሆን ሌላው በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ማስመዝገብን የሚመለከት መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በጠቅላላ ጉባዔ የመሳተፍ መብት የሚጀምረው አዲስ ኩባንያ ከሆነ አክሲዮን ከተገዛበት ጀምሮ ሲሆን ከሌላ ባለአክሲዮን መተላለፍን በሚመለከት በሰነዶች ምዝገባ ከተመዘገበ በኋላ እንደሆነከገለፁ በኋላ ያቀረቡት ጥናታዊ ፅሁፍ ምንም እንኳ በተወሰኑ ድንጋጌዎች ላይ ቢሆንም በይዘት ደረጃ ጥልቅና አከራካሪ መሆናቸውን በማስታወስ ገለፃቸውን ቋጭተዋል፡፡

## አቶ ማርሻል ፍቅረማርቆስ - አወያይ (የሕግ አማካሪና ጠበቃ የቀድሞ ቡና ኢንተ. ባንክ የቦርድ ሊቀመንበር)

ጽሑፍ አቅራቢ አቶ ኃይሉ ቡራዩን ከልብ ካመሰገኑ በኋላ የንግድ ሕጉ ከውክልና መስጠት ጋር ተያይዞ ዝርዝር አፈፃፀሞች ላይ ብዙ ችግር እንዳለ አብራርተዋል፡፡ በቦርድ አባላት እና በባለአክሲዮኖች ውክልና መስጠት ጋር ተያይዞ ልዩነት ያላቸው መሆኑን በምክር ቤት ወይም በቦርድ አባል የሚሰጥ ውክልና ሌላ የቦርደ አባል እንጂ ለሌላ ሦስተና ወገን መስጠት የማይቻል እንደሆና በዳይሬክተሮች ቦርድ (የኩባንያ ምክር ቤት) መካከል የሚደረግ ውክልና ላይ በመካከላቸው ብቻ እንዲቀር የተደረገበትን አመክኖ (rationality) ሲያብራሩም በቦርድ አባል የሚደረገው ውይይት እና የሚተላለፈው ውሳኔ በሚስጥር መጠበቅ መርህ (principle of confidentiality) የተሞላ በመሆኑ ይህን ውስጣዊ ገመና በውክልና ምክንያት የውጭ ሰው ለሆነ ሦስተኛ ወገን መተላለፍ የሌለበት መሆኑ ቀዳሚው ሲሆን ሌላኛው ደግሞ የቦርድ አባል ሲመረጥ የሌሎች ንብረት የሆነን አክሲዮን ወይም ቁሳዊ ጥቅም ከፍ ባለ ጥንቃቄ የማስተዳደር ኃላፊነት(fiduciary duty) መርህን በአግባቡ እንዲወጣ የሚመረጥ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ለሦስተኛ ወገን ውክልና መስጠቱ አግባብ አለመሆኑን

እንደምክንያት አስቀምጠዋል፡፡ የባለአክሲዮኖች ውክልና መስጠትን በተመለከተ ግን ከላይ ተጠቀሱትን ዓይነት ክልከላዎች የሌሉበት ሲሆን ባለአክሲዮኖች እንደየምርጫቸው ለሌላ አባል ወይም ለሦስተኛ ወገን ፕሮክሲውን ሊሰጡ እንደሚችሉ ገልፀዋል፡፡

የእንደራሴነት ሥልጣን የሚተረጎመው ሳይስፋፋ በጠባቡ መሆን እንደለበት የፍትሓብሔር ሕጉ በአንቀፅ 2181 (3) ሥር የተመለከተ መሆኑን ገልፀው እንደራሴ ሿሚው በማንኛውም ጊዜ በእርሱ ስም ሆኖ እንዲሰራ የሰጠውን ስልጣን ሊቀንስበት ወይም ሙሉ ለሙሉ ሊያስቀረው እንሚችልና ይህን መርህ የሚፃረር በውክልና ውሉ ላይ የሚሰፍረው ማንኛውም ጽሑፍ ፈራሽ እንደሆነ በፍትሐብሔር ሕጉ በአንቀፅ 2183 ሥር የተመለከተ መሆኑን በመግለፅ ወካይ በፈለገ ጊዜ በሶስተኛ ወገን ፊት የሚሰጠው ውክልና የመሻር ወይም የሥልጣኑን መጠን ሊቀንስ የሚችል መሆኑን አብራርተዋል፡፡

አንድ ተወካይ የብዙ ባለአክሲዮኖችን ሥልጣን በውክልና መውሰድ ሊሠራበት የሚችል በሆንም ይህ ነፃነት ግን አሁን በብሔራዊ ባንክ ገደብ የተጣለበት ይመስለኛል ብለዋል፡፡ በእንግሊዝ እና በደቡብ አፍሪካ የሕግ ሥርዓት ውክልናን በሚመለከት ወካይ ፕሮክሲን ሊሽር ከሚችልበት ሁኔታዎች መካከል አንዱ ወካዩ በጠቅላላ ጉባዔው ላይ ተገኝቶ በራሱ ድምፅ ሲሰጥ እንደሆነ ያስቀምጣሉ፡፡ የውጭ ሀገራት በውክልና የሚተላለፉ ሥልጣኖች ተለይተው የተቀመጡ ሲሆን እነዚህም:-

1. የመናገር ሥልጣን (speak)
2. የመሳተፍ (attend) እና
3. የመምረጥ (vote)

እንደሆኑ ገልፀው በነዚህ ሀገራት ለምሳሌ በተራ ቁጥር 1 እና 2 ሥር የተጠቀሱትን በውክልና በማስተላለፍ 3ኛውን ሥልጣን ለራሳቸው የሚያስቀሩበት ሁኔታ መኖሩን ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ዓይነት ክፍፍል በእኛ ሀገር የውክልና ሕግ ላይ የሌለ ሲሆን ተወካይ በስብሰባ ላይ ይሳተፋል የሚል በጥቅል የተቀመጠ ነገር ግን ሦስቱንም ሥልጣኖች በውስጡ የሚያጠቃልል እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

በገለጻው ተነስቶ የነበረው ሌላው መሠረታዊ ጥያቄ ደግ ከምክር ቤት አባልነት ምርጫ ጋር በተያያዘ አንድ ተወካይ በስብሰባው ላይ ሲሳተፍ ለቦርድ አባልነት እጩ ሆኖ ቢጠቆም ሊመረጥ ይችላል ወይ የሚለውም ለውይይት የሚሆን መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በአንድ አንድ አክሲዮን ማህበራት የባለአክሲዮኑ ቁጥር እጅግ ብዙ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ የቃለ-ጉባዔ ፀሐፊ ለመምረጥ፣ አጀንዳ ለማፀደቅ ወዘተ በጭብጨባ ድምፅ የሚሰጥበት አግባብ አለ፡፡ ይህ ዓይነቱ

አካሄድ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አባላት ባሉበትና ዋና ዋና በማይባሉ ውሳኔዎች ላይ ብቻ የሚገለገሉበት ሲሆን በዚህም ሁኔታ ቢሆን ልዩነት ያላቸው ሰዎች ልዩ አቋማቸውን በማስመዝገብ ከብዛታቸው አንጻር ተገምግሞ አብላጫ የሚሆኑ ከሆነ ውሳኔው የሚሻር መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

ወካይ ተወካይን ለመታዘብ ወደ ጠቅላላ ጉባዔ ቦታ ሄዶ መታደም ይችላል አይችልም የሚለውን በተመለከተ በደባልነት የመቀበል ልምድ በተግባር የሌለ መሆኑን በጉባዔው የሚነሱ ውይይቶችና ውሳኔዎች ሚስጥራዊነትን መጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ እንደሆነ እና ማንኛውም ሰው የሚገባበት አለመሆኑን ጨምረው ገልፀዋል፡፡ ከላይ ከነሷቸው ነጥቦች ውጭም በገለፃው የተነሱ መወያያ ጥያቄዎች ያሉ በመሆኑ በውይይት እንዲዳብር በሚል መድረኩን ለተሳታፊ ክፍት አድርገዋል፡፡

## አቶ ደበስ ትኩዕ - ከአንበሣ ኢንተርናሽናል ባንክ

የቀረበው ፅሁፍና ገለፃ በጣም ጥሩ እንደሆነ ገልፀው ምስጋናቸውን ካቀረቡ በኂላ በሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ ጽ/ቤት የሚሰጥ ልዩ የውክልና ሥልጣን ለ3 ዓመት ብቻ የሚያገለግል ስለመሆኑ የሕግ ድጋፍ ያለ እንደሆነ እንዲጠቀስላቸው ከጠየቁ በኂላ የፍትሓብሔር ሕጉ አንቀፅ 2206 መሠረት ልዩ ውክልና የተሰጠው ሰው ሥልጣን ለጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ እንዲሳተፍ እንደሆነ ሦስቱንም ሥልጣኖች ማለትም የመናገር፣ የመሳተፍ/የመታደም እና የመምረጥ ሥልጣንን ያካተተ እንደሆነ የራሳቸውን አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

## አቶ ቴዎድሮስ ምህረት - ከኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር

የውክልና መስጫ ሰነድ በአዋጅ ቁጥር 922/08 መሠረት በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ፅ/ቤት መረጋገጥ ያለበት መሆኑ ይታወቃል፡፡ የፕሮክሲ ሰነድ በኩባንያው ውስጥ በሚገኝ ፎርም መሰረት የተመዘገበ እንደሆነ ከዚህ አዋጅ አንፃር በሕግ ፊት ሊፀና የሚችል ዋጋ ያለው ሰነድ ነው ወይ? የአክሲዮን ማኅበራት ጠቅላላ ጉባዔ ላይ ለመሳተፍ የሚሰጥ ውክልና ልዩ ነው ሊባል ይችል ይሆናል፤ ነገር ግን ይህ አዋጅም በቅርብ የወጣ እና ልዩ ሕግ ነው በማለት ጥያቄያቸውን ይበልጥ አጠናክረዋል፡፡

## አቶ ኃይሉ ሞላ - ከኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር

የንግድ ሕጉ አንቀፅ 358 ብዙ ጊዜ ኩባንያዎችን ያጨቃጭቃል፡፡ ፎርማቱ በግልፅ አልተቀመጠም፡፡ አንዳንዴ ውክልና በቃል የሚሰጥበት ሁኔታ አለ፡፡ የውክልና የጊዜ ገደብ እንኳ አይቀመጥም፡፡ በቅርብ በሚሻሻለው የንግድ ሕግ ላይ ምን ትላላችሁ?

## አቶ አርዓያ ከበደ - የሕግ አማካሪና ጠበቃ

የተወካይ በጠቅላላ ጉባዔ ላይ የመሳተፍ የሥልጣን አድማስን አስመልክቶ አስተያየት ለመስጠት እንደሆነ ገልፀው ተወካይ የተሰጠው ሥልጣን ‹በስብሰባው መሳተፍ› የሚል እንደሆነ መናገርንም ድምፅ መስጠትንም ማካተት አለበት የሚል እምነት እንዳላቸው ይሁን እንጂ በውክልና ውሉ ላይ በግልፅ የሚከለክሉ ወይም ሥልጣን የሚነፍጉ አንቀፆችን ግን ማክበር ተገቢ እንደሆነ በመግለፅ በሕንድ ሀገር አንድ ተወካይ በጉባዔ መናገር የማይችል ስለመሆኑ የነበረውን ልምድ የተወካይ ንግግር ኩባንውን ወይም የሌሎች አባላትን ስሜት ሊጎዳ ይችላል ወይም ደግሞ እንደወካዩ ሆኖ በወካዩ አንደበት አይናገርም ቁማናቸውም አካላቸውም አንድ ባለመሆኑ የሚለው አሳማኝ አለመሆኑን ገልፆ ይልቁንም ተወካይ የወካዩን ጥቅምና ፍላጎት በተቻለ መጠን ለማሟላት የሚተጋ እንጂ የኩባንያውን ወይም የሌሎችን አባላት ጥቅም ለማስጠበቅ አለመሆኑን አስረግጠው አስረድተዋል፡፡ በተጨማሪም ወካይ ውክልና ሰጥቶ ነገር ግን በጉባዔው ላይ ከተገኘ ውክልና የተሰጠው ሰው ቢኖር እንኳ የወካይ ባለአክሲዮን በጉባዔው የመሳተፍ ሥልጣን ሊነፈግ አይገባውም ብለዋል፡፡

## አቶ ሰማኸኝ/ሰማው

በአክሲዮን ማኅበሩ ወይም በኩባንያው ውስጥ የሚካሄድና በዚሁ ማኅበር የሚመዘገብ ሽያጭ ወይም ማንኛውም ስመንብረትን ወደሌላ ሰው የሚያስተላለፍ ሁኔታ ሕጋዊ ዋጋ እንዲኖረው የግድ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ፊት መመዝገብ አለበት? የሚል ጠያቂ በማንሳት በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መካከል ላለው ግንኙነት ሽያጭ መኖሩ ብቻ በቂ እንደሚመስላቸው ይልቁንም ምዝገባ የሚያስፈልገው ከሦስተኛ ወገን ጋር ባለው ግንኙነት ጥቅም ላይ የሚውል እንደሆነ አክለዋል፡፡

በተጨማሪም አክሲዮን ማኅበራትን አስመልክቶ ውክልና የተሰጠው ሰው ወኪሉ ተገኝቶ እኔ እርሱን ወክዬ ለመመረጥ እችላለሁ ወይም የኔ principal የኩባንያው ምክር ቤት ወይም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሆኖ መመረጥና ይፈልጋል ማለት ይችላል፤ ሌላው ከባልና ሚስት አንደኛው ወገን ባለአክሲዮን ሆኖ ሌላኛውን ውክልና ሊሰጥ ይችላል፤ አሊያም ሞግዚትና አሳዳጊዎች በልጆቻው ስም

አክሲዮን የሚገዙ ሆነው አነሱን ወክለው በእንደራሴነት የሚቀርቡ ሰዎች የቦርድ አባል ሆነው እንዳይመረጡ የሚከለክል የሕግ አግባብ መኖር አለመኖሩ እንዲገለፅላቸው ጠይቀዋል፡፡

## አቶ ኃይሉ ቡራዩ - ጽሑፍ አቅራቢው የሰጡት ምላሽ

የቀረቡ ጥያቄዎች ላይ ሃሳባቸውን የሰጡ ሲሆን በልዩ ውክልና ላይ የተቀመጠው የ3 ዓመት የጊዜ ገደብ በፍ/ብሔር ሕጉ አንቀፅ 2204 ላይ የተጠቀሰው መኖሩን ጠቁመው በአክሲዮን ማህበር ውስጥ ለሚደረግ ሽያጭ ኩባንያው ባዘጋጀው ፎርም ተሞልቶ በዳይሬክተሮች ቦርድ ተመርምሮ የፀደቀ እንደሆነ ልዩ ምዝገባ እንደማያስፈልግ ገልፀዋል፡፡ ውክልና በቃል መስጠት ፈፅሞ እንደማይቻልና ይህ በሚሆንበት ጊዜ ምንም ዓይነት ሕጋዊ ውጤት እንደማይኖረው ውክልና በፎርም ተሞልቶ እተመዘገበ የሚሄድ ሲሆን ለጠቅላላ ጉባዔ ተሳትፎ በኩባንያው የሚሞላ ኩባን ለአንድ ጠቅላላ ጉባዔ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውል መሆኑን ተወካይ በወረቀት ድምፅ ከመስጠት ባለፈ በመናገር ተሳታፊ መሆን አለመሆኑ እንደጥያቄ አንስተዋል፡፡

የአክሲዮን ሽያጭ በ2 መልኩ የሚፈፀም ወይንም የአክሲዮን ዓይነቶች 2 መሆናቸውን ጠቅሰው አነርሱም፡-

1. ላምጪው (bearershare) እና
2. በስሙ የሚመዘገብ (registered share)

እንደሆኑ ገልፀው ላምጪው (bearershare) በሕጉ ላይ የተጠቀሰ ቢሆንም በተግባር የማንጠቀምበት መሆኑን፤ በሀገራችን አክሲዮን መመዝገብ እንዳለበት ገልፀው ባለአክሲዮን መምረጥም ሆነ መመረጥ የሚችለው ከዚህ በኂላ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

## አቶ ማርሻል ፍቅረማርቆስ - አወያይ (የሕግ አማካሪና ጠበቃ የቀድሞ ቡና ኢንተ. ባንክ የቦርድ ሊቀመንበር)

የባለአክሲዮኖች ስብሰባ ላይ የተወከለ ሰው የሥልጣን ወሰኑ በፍትሓብሔር ሕጉ አንቀፅ 2206 ሥር የተቀመጠው ሲሆን አንቀፁም እንሚከተለው ነው፡፡

*__አንቀፅ 2206፦ ልዩ ውክልና የተሰጠው ሰው ሥልጣን__*

*(1) ልዩ ውክልናው በላዩ ተዘርዝረው የተመለከቱትን ጉዳዮችና የነዚሁ ተከታታይና ተመሳሳይ የሆነውን እንደ ጉዳዩ ዓይነትና እንደ ልማድ አሠራር አስፈላጊ የሆነውን ከማከናወን በቀር ለተወካዩ ሌላ ሥልጣን አይሰጠውም፡፡*

*(2) ተወካዩ ከተሰጠው የውክልና ሥልጣን ውጭ አልፎ የፈፀመውን የሥራ ተግባር ወካዩ ካላፀደቀው ወይም በሥራ አመራር መሠረታዊ ደንብ ካልሆነ በቀር ወካዩን አያስገድደውም፡፡*

አንድ ባለአክሲዮን ፕሮክሲ ሰይሞ በጠቅላላ ጉባዔ እንዲሳተፍ ሥልጣን ሰጥቶ ያዘዘው እንደሆነ ከላይ በተጠቀሰው የሕግ አግባብ መሠረት ተወካዩ ወካይ ሊኖረው የሚችለውን ሥልጣን ይኖረዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡ የእንደራሴነት ሥልጣን የሚተረጎመው ሳይስፋፋ በጠባቡ መሆን እንደለበት የፍትሐብሔር ሕጉ በአንቀፅ 2181 (3) ሥር የተመለከተ መሆኑን ቀደም ብለን የተመለከትን መሆኑን አስታውሰው አንድ ተወካይ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሆኖ ሊመረጥ ይችላል የሚል እምነት የለኝም ብለዋል፡፡

የአክሲዮን ማህበር አስተዳዳሪዎች ማለትም የቦርድ አባላት ኩባንያውን መሠረታዊ ህልውና የማስጠበቅ ከፍተኛ ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን ኩባንያዎች የየራሳቸውን የዳይሬክተሮች ቦርድ ውስጠደንብ ያለ ሲሆን ይህ ደንብ ዝርዝር የሆኑ ነገሮችና የሚያስቀምጥ ሲሆን አንድ የቦርድ አባል ቢያንስ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ምን ያህል የቦርድ ስብሰባዎችን መሳተፍ እንዳለበት ያስቀምጣል፡፡ በመሆኑም አንድ የቦርድ አባል ዝም ብሎ ውክልና ሰጥቶ ይጠፋል ማለት እንዳልሆነ አስረድተዋል፡፡ በውስጥ አሠራር እና ሥርዓቶች የቦርድ ጉዳይን በተመለከተ ውክልና በፅሁፍ ሊሰጥ የሚችል መሆኑ ቢደነገግ መልካም እንደሆነ ገልፀው በrepresentative እና በproxy መካከል ልዩነት እንዳለ ጠቁመው በሕግ ሰውነት የተሰጣቸው አካላት ባለአክሲዮን ወይም የቦርድ አባል ሆነው ሊቀርቡ የሚችሉ ሲሆን እነዚህን አካላት ወክሎ በአካል የሚመጣው የተፈጥሮ ሰው representative የሚባል ሲሆን በዚህ አኳኋን የሚመጣው ሰው የቦርድ አባል ሆኖ ሊመረጥ የሚችል ሲሆንproxy ማለት እስካሁን ስንነጋገርበት የቆየነው የተፈጥሮ ሰው እንደሆነ አብራርተዋል፡፡ የሞግዚት እና የባልና ሚስት በቦርድ አባልነት እጩ ሆኖ የመመረጥ ክርክር እንደቅደምተከተላቸው ንብረት የማስተዳደር እና የጋራ ንብረት ግምት እስከምርጫ ድረስ ተለጥጦ ሄዶ አከራካሪ ሊሆን ይገባዋል ወይ የሚል ጥያቄ አዘል አስተያየታቸውን አስቀምጠዋል፡፡

## ዶ/ር ኤልያስ ኑር - ከሚዛን ሎው ሪቪው

ተወካይ ውል ሲገባ ወካይን ወክሎ ልክ እንደርሱ ሆኖ ለመስራት መሆኑ የሚታመን ነው ካሉ በኋላ ተወካይ የሚሰራው በእራሱና ለራሱ ሳይሆን ወካዩን መስሎ ለወካዩ ሁለንተናዊ ጥቅምን ለማስጠበቅ እስከሆነ ድረስ ወካይ ለምክር ቤት ወይም ለቦርድ አባልነት እጩ ሆኖ ሲመረጥ እንደ ባለአክሲዮን ወካይ ተመራጭ መቅረቡ አግባብ ነው ነው ምክንያቱም እርግጥ ነው ፕሮክሲው የወካዩን ስብዕና፣ ማንነት፣ እውቀት እና ክህሎት፣ ማኅበራዊ ተግባቦት ወዘተ ግላዊ ባህሪያትን ባይወክልም ዞሮዞሮ በቦርድ አባልነት የሚሰራው ወካዩ በመሆኑ በዛች የስብሰባ ቀን በመቅረቱ ብቻ ይህ መብቱ ሊታለፍ አይገባውም የሚመረጠው ወካዩ እስከሆነ ድረስ በማለት ምላሻቸውን ከማብራሪያ ጋር አስቀምጠዋል፡፡

## አቶ ተስፋዬ አሰፋ - ከሰነዶች ምዝገባ እና ማረጋገጫ ፅ/ቤት

ቀደም ብሎ ከመድረኩ የተነሳ ቢሆንም አፅንዖኦት ለመስጠት ያህል የኩባንዎችን ቃለጉባኤ በተለይም ከሦስተኛ ወገን ጋር የሚያገናኝ፣ የመመስረቻ ፅሁፍና የመተዳደሪያ ደንብን የሚለውጥ በሆነ ጊዜ ይህንኑ የመመዝገብ ኃላፊነት የሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ፅ/ቤት እንደሆነ ገልፀው የዕለት ተለት ሥራን የሚመለከቱ ቃለጉባዔዎች ግን የማይመዘገቡ መሆኑን መሠረታዊ ለውጥን የሚያመጡ ለምሳሌ የአክሲዮን ሽያጭ መመዝገብ እንዳለበት በርግጥ ሽያጭ የሚከናወነው በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መካከል ቢሆንም የባለአክሲዮኖች ፈቃድ እና ስምምነት መኖሩ የሚረጋገጠው በምዝገባ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

## አቶ ውበቱ አሠፋ - ከቡና ኢንተርናሽናል ባንክ

በንግድ ሕጉ አንቀፅ 398 እና በአዋጅ ቁጥር 922/08 መካከል ተቃርኖ ያለ ይመስለኛል፡፡ ውክልና በተለያዩ ተቋማት የሚሰጥ መሆኑ ይታወቃል ከነዚህም መካካል ውክልና በቆንፅላ ፅ/ቤቶች፣ በማረሚያ ቤቶች፣ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤቶች ወዘተ. አክሲዮን ደግሞ ከባለአክስዮኑ ወደ ሌሎች ሰዎች በተለያየ አግባብ የሚተላለፍ ሲሆን በሽያጭ፣ በውርስ፣ በስጦታ ወዘተ በአክሲዮን ማኅበሩ ዋና መዝገብ ላይ ተመዝግቦ ሊከናወን ይችላል፡፡ እነዚህን ዐይነት ባለቤትነትን ወደ ሌላ የሚያስተላልፉ ውሎች የግድ ይመዘገባሉ ማለት አይደለም፡፡ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላነትን በውክልና የመመረጥ ጉዳይን በተመለከተየሚከለክል ሕግ የሌለ በመሆኑ ወካይ ባይገኝም ኤክስፐርቲዙን እንፈልጋለን ካሉ መመረጥ ይችላል የሚል እምነት አለኝ ብለዋል፡፡

## አቶ ኤልያስ ተ/ብርሃን - ከኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር

ከተሰጠው ሥልጣን አልፎ መስራትን (ultravirus) በተመለከተ ምንም እንኳ በንግድ ሕጉ ላይ ያልተመለከተ ቢሆንም አንድ ተወካይ በውክልና ውል፣ በሕግና እንደ ልማድ አሠራር አስፈላጊ ሆኖ ከተሰጠው ሥልጣን አልፎ የሰራ እንደሆነ በፍትሓብሔር ሕጉ የእንደራሴነት ክፍል እንደተመለከተው ወካይ ይህንኑ አድራጎት የተቀበለው እንደሆነ የሚፀና ሲሆን (የፍትሓብሔር ሕጉ አንቀፅ 2207) በሌሎች ሀገራት ያለው ተሞክሮ ወካዩ ከሥልጣኑ ውጭ የከወነው ሥራ የሚፀና ሆኖ ውክልናውን ለመሻር እንደ በቂ ምክንያት ይቆጠራል ብለዋል፡፡

አክሲዮኖች እንደ ማንኛውም ንብረት የዕዳ መያዣ ሆነው ለባለገንዘብ ሊሰጡ የሚችሉ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን በንደዚህ ዓይነት ሁኔታ አክሲዮኑ የተያዘበት ባለአክሲዮን በጠቅላላ ጉባዔ ላይ የመሳተፍ ሁኔታ በፍትሐብሔር ሕጉና በንግድ ሕጉ መካከል መሠረታዊ የሆነ ተቃርኖ መኖሩ የሚታወቅ ሲሆን አንድ ባለአክሲዮን ምንም እንኳ የአክሲዮን ባለቤት የአክሲዮን ሰርተፊኬቱን በመያዣነት አሳልፎ ቢሰጥም ንብረትነቱ አሁንም ቢሆን በአባሉ ስም የሚቆይ በመሆኑ፣ ትርፍ የሚከፈለው ለአባሉ በመሆኑ እንዲሁም በመያዣነት አክሲዮኑን የያዘው ባለገንዘብ ስለ አክሲዮን ማህበሩ የሚያውቀው ነገር የሌለ በመሆኑ በጠቅላላ ጉባዔ ላይ መሳተፍ ያለበት እራሱ ባለአክሲዮኑ እንጂ በመያዣነት የያዘው ሰው መሆን እንደሌለበት ጠቅሰው የንግድ ሕጉ በዚህ ረገድ መሻሻል እንዳለበት ጠቁመዋል፡፡

## አቶ ፋሲል ስለሺ - ከኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር

ከባለአክሲዮንነት እና ከውክልና ጋር በተያያዘ የባልና ሚስትን ግንኙነት ሕጉ እንደሚያየው በሁለት መንገድ ከፍሎ ማየቱ ተገቢ ይመስለኛል፡፡ ባልና ሚስት አንድም ግላዊ ግንኙነት (personal relation) አንድም የንብረት ግንኙነት (pecuniary relation) ግንኙነት አሏቸው ስለሆነም ይህን ለይተን ብንመለከት የሚል ነጥብ ካነሱ በኋላ ከአክሲዮን ምዝገባ ጋር በተያያዘበንግድ ሕጉና በአዋጁ መካከል ያለውን ተቃርኖ ወደ ትርጓሜ ቅኖናዎች በማምራት ልዩ ሕግ ከጥቅል ሕጉ የተሻለ ተመራጭ መሆን መርህን (special law prevail over the general) ወይም የአሁኑ ሕግ ከቀድሞው የተሻለ ተመራጭ መሆን መርህን (later law prevail over the former) መጠቀም አዋጭ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

## አቶ ቴዎድሮስ ምህረት - ከኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማህበር

የውክልና ሰነድ ሕጋዊነት የጊዜ ገደብን በተመለከተ የተቀመጠው የፍትሓብሔር ሕጉ አንቀፅ 2204 እንደሚከተለው ይነበባል፡፡

*አንቀፅ 2204፡- የአስተዳደር ሥራ*

(1) *የወካዩን ሀብት የማስቀመጥ የመጠበቅ ከሦስት ዓመት ለማያልፍ ዘመን የማከራየት፤ በብድር ተሰጠውን ሀብት የመሰብሰብ፤ ከሀብቱ የሚመጣውን ገቢ ተቀብሎ የማስቀመጥና ለተከፈሉ ዕዳዎች ደረሰኝ የመስጠት ሥራዎች ሁሉ እንደ አስተዳደር ሥራ ይቆጠራሉ፡፡*

በንግድ ሕጉ ላይ ያለው ፕሮክሲ ሲሆን በፍትሐብሔር ሕጉ ላይ ያለው ኤጀንሲ (power of attorney) ነው፡፡ ውክልና የሚሰጠው አንድም በኩባንያው ፊት በተጋጀ ፎርም መሠረት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ፊት የሚደረግ ውል ነው፡፡ በኩባንያው ሕጋዊ አዋዋይ ፊት በቅፁ መሠረት የሚፈፀመው የውክልና ውል ወይም ፕሮክሲ ለጠቅላላ ጉባዔ ተሳትፎ የሚያገለግል ሲሆን በሰነዶች ምዝገባ ፊት የሚደረገው ውክልና የጊዜ ገደብን ግን በሁለት መንገድ ከፍሎ ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በፍ/ብሔር ሕጉ አንቀፅ 2204 (1) ሥር የተቀመጠው የ3 ዓመት የጊዜ ገደብ የአስተዳደር ሥራ ምን ማለት እንደሆነ ለመተርጎም የተቀመጠና እና ከኪራይ ጋር የተገናኘውን የጠቅላላ ውክልና ክፍል መሆኑን ነገር ግን ከአክሲዮኖች ጋር በተያያዘ በሰነዶች ምዝገባ የሚሰጥ ልዩ ውክልናን በተመለከተ ምንም ዓይነት የጊዜ ገደብ በሕጉ ያልተቀመጠ መሆኑን እና ውሉ በጊዜ ገደብ ሳይሆን ወካይ ውክልናውን ሲሽር፣ ወኪሉ የውክልና ሥልጣኑን ሲተው፣ የተወካይ ወይም የወካይ መሞት ወይም ሥራ ለመቻል ወዘተ ውክልና መቅረት ምክንያቶች ናቸው፡፡

በሌላ ጉዳይ ደግሞ በአንድ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ ወኪል ሆኖ የቀረበ ሰው ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት መመረጥ አይችልም የሚል አቋም እንደሌላቸው ይልቁንም ወኪሉ በተኘበት ወካይ ለቦርድ አባልነት ቢመረጥ የሚመረጠው በመገኘት አለመገኘቱ ሁኔታ የሚወሰን ሳይሆን የተመራጩ አቅምና ማንነት ከመሆኑም ባለፈ አንድ ሰው ለቦርድ አባልነት ምርጫ የሚቀርበው በቅድሚያ በኩባንያው ውስጥ ባለአክሲዮን መሆኑን መዘንጋት እንደሌለብን ጠቁመዋል፡፡

ተወካይ በአክሲዮን ማህበር ጠቅላላ ጉባዔ ላይ እንዲሳተፍ ከባለአክሲዮኑ ውክልና ተሰጥቶት በስብሰባው ላይ የሚኖረው ሥልጣን እና መብት በውሉ ላይ እስካልተገደበድረስ ከወካዩ ባለአክሲዮን እኩል መሆን እንዳለበትና በንግድ ሕጉ አንቀፅ 389 ላይ የተመለከቱት የባለአክሲዮን መብቶች ሙሉ

በሙሉ የማኅበሩን ውሳኔ እስከመቃወም ድረስ ሊኖሩት ይገባል ያሉ ሲሆን የጠቀሱት የሕግ አንቀፅም እንደሚከተለው ይነበባል፡፡

*<u>አንቀፅ 389፡- የባለአክሲዮኖች የራሳቸው የሆኑ መብቶች</u>*

(1) *በቁጥር 388 የተመለከተው ቢኖርም እንኳ ባለአክሲዮኖች በየራሳቸው ፈቃድ ካልሆነ በቀር በማህበርተኝነታቸው ያሏቸው መብቶች ሊቀሩባቸው አይችሉም፡፡*

(2) *እንዳገኟቸው የሚቆጠሩት መብቶች በሕግ ወይም በማኅበሩ መመስረቻ ጽሁፍ ወይም መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ከጠቅላላው ጉባዔ ወይም ከአስተዳዳሪዎች ውሳኔዎች ጋር ግንኙነት የሌላቸው ወይም በጠቅላላው ጉባዔ ተካፋይ ለመሆን ካላቸው መብት የሚመነጨት ናቸው፡፡ ይኸውም በተለይ ማኅበርተኛ የመሆን መብት፣ ድምፅ ማግኘት መብትና የመስጠት መብት፤ ማኅበሩ ውሳኔ የመቃወም መብት፤ እንዲሁም የትርፍን ድርሻና ማኅበሩም ሲፈርስ በመጨረሻ በሚደረገው በሒሳብ ማጣራት ጊዜ ድርሻን የመክፈል መብት ነው፡፡*

ይህን ከተነተኑ በኋላ ባልና ሚስትን በሚመለከት አክሲዮን የጋራ ንብረት ሲሆን ይህ ሁኔታ በሁለቱ መካከል ባለው ግንኙነት ነው እንጂ በሦስተኛ ወገን (በኩባንያው) ላይ መሆን የለበትም በማለት አንድ ሞግዚትም እንደ አክሲዮን ባለቤት ልጆችን ወክሎ መመረጥ እንደሌለበት ገልፀዋል፡፡

## <u>አቶ ሰማኸኝ/ሰማው</u>

ወኪል የወካይን ጥቅምና ፍላጎት ለማስቀጠል (advance the interest of the principal) ጥብቅ በሆነ ቅንነትና ትጋት እንደሚሰራ የሕግና የመርህ ግዴታ ያለበት በመሆኑ ወኪሉ ላይ የሕግ ክልከላዎች ከሌሉ በቀር ክልከላ ልናደርግበት አይገባም ብለው ባልና ሚስትን በሚመለከት የአክሲዮን ንብረትን በተመለከተ እያንዳንዳቸው 50 በመቶ ድርሻ እንዳላቸው ግምት የሚወሰድበት በመሆኑ ባል በቦርድ አባልነት ቢመረጥ ባለአክሲዮን ተብላ የተመዘገበችው ሚስት በመሆኗና ባል ስም ተመዝግቦ የሌለ በመሆኑ ምክንያት ልትመረጥ አይገባም ሊባል እንደማይቻል አቋማቸውን አንፀባርቀዋል፡፡

## <u>አቶ ብሩ ኪዳኔ- የሕግ ባለሙያ</u>

ባበልና ሚስት ጉዳይ እና በሌሎችም አካባቢዎች የተነሱ ነጥቦች ጥሩ ናቸው፡፡ ባል ወይም ሚስት በግል ሀብታቸው የገዙት አክሲዮን ላይ ሌላኛው ወገን (the other spouse) ውክልና ተሰጥቶት ቢመረጥ ምን ይሆናል በሚል ጥያቄ አንስተዋል፡፡

## አቶ ማርሻል ፍቅረማርቆስ - አወያይ

በአክሲዮን ማህበራት ጠቅላላ ጉባዔ ላይ የሚነሱ አከራካሪ ጉዳዮች እዛው ተፈተው እንዲያልቁ ነው የሚደረገው፡፡ በእርግጥ የባልና ሚስት ንብረት የህግ ግምቱ የጋራ እንደሆነ ይታወቃል ነገርግን ይህ ዓይነት እና ሌሎችም በስብሰባው የሚነሱ ለክርክር የሚያጋልጡ ሁኔታዎች ሲገጥሙ ወይም ሲኖሩ ችግር ያለበትን ገለል በማድረግ የጠራው ነው ተመራጭ የሚሆነው ይህ አካሄድ በአስተዳደር የሚመከር መሆኑን እና የባልና የሚስት ወይም የሞግዚትነት ክርክር የሚያስነሱ ያልጠሩ ሁኔታዎችን በተቻለ መጠን አለማስተናገድ ተመራጭ ሊሆን ይችላል በማለት የመፍተሔሃሳብ ጠቁመው በንግድ ሕጉ አንቀፅ 420 (2) አሁንም እንደጥያቄ እንዲያዝለት ጠይቋል፡፡

## አቶ ታምራት ኪዳነማርያም - ከኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር (ፕሬዚዳንት)

በቀረበው ጥናታዊ ጽሁፍ፣ በተነሱ የመወያያ ጥያቄዎች እና በቤቱ የተነሱ ሃሳቦች ብዙና ሰፊ ናቸው፡፡ በተነሱ አንኳር ነጥቦች ላይ መግባባት ላይ የተደረሰባቸው እንዳሉ በምሳሌነትም በምክር ቤት ወይም በዳይሬክተሮች ቦርድ የመመረጥን ሁኔታ አስመልክቶ እንደራሴው ሿሚውን ወክሎ የሚቀርብ በመሆኑ ምርጫው የሚመለከተው ወካዩን መሆኑን የሞግዚትነቱን በተመለከተ ሕፃናት የአክሲዮን ባለቤት በሚሆኑበት ጊዜ ቤተሰብ ሊመረጥ ይችላል የሚለው አከራካሪ እንደሆነ ነገር ግን ልጆች እራሳቸው የአክሲዮን ባለቤት በመሆናቸው ብቻ የቦርድ አባል ይሆናሉ ማለት ግን አስቸጋሪ እንደሚሆን አስቀምጠዋል፡፡

## አቶ መስፍን ጌታቸው - ከብሔራዊ ባንክ

የንግድ ሕጉ አንቀፅ 420ን በሚመለከት ውስን ቁጥር ያላቸው ባለአክሲዮን ብቻ ላሉት አክሲዮን ማህበር ጠቃሚ ይሁን እንጂ በብዙ ሺዎች ለሚቆጠሩ አባላት ላለው ኩባንያው አንቀፁ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ የውጭ ሀገራት ተሞክሮን ስንመለከት በሕንድ እና በእንግሊዝ ሀገር company የሚለውን በሁለት መልኩ የሚያዩት ሲሆን እነዚህም፡-

1. Private company፡- አንድ ተወካይ የመታደም፣ የመናገር እና የመምረጥ መብት ወይም ሥልጣን ይሰጣሉ፡፡
2. Public company፡- በዚህኛው የኩባንያ ዘርፍ ውስጥ በሚመደቡት ግን አንድ ተወካይ ድምፅ መስጠት የሚችለው በመናገር ሳይሆን በወረቀት ብቻ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

በእኛ ሀገር ባለአክሲዮን አንድ ወኪል ብቻ የሚሰይም ሲሆን ወኪሎች ግን ከብዙ ባለአክሲዮኖች ውክልና ወስደው የሚሰሩ ይሁን እንጂ ወኪል ሆነው የሚሰሩላቸው ባለአክሲዮኖች የአክሲዮን ብዛት መሰረት ገደብ የተደረገበት ሲሆን ይህም እስከ 10 በመቶ የኩባንያው ፔይድ አፕ ካፒታል ድረስ ብቻ ውክልና መውሰድ እንደሚችሉ በአዋጅ ተደንግጓል በማለት አብራርተዋል፡፡

## አቶ ማርሻል ፍቅረማርቆስ - አወያይ

ለጽሑፍ አቅራቢውና ለተሳታፊ ባለሙያዎች እንዲሁም መድረኩን ላዘጋጀው ለኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ምስጋናቸውን አቅርበው የትምህርታዊ ውይይቱ ያበቃ መሆኑን ተናግረው የማኅበሩ ፕሬዝዳንት በመጨረሻም መናገር ያለባቸው ነገር ያለ እንደሆነ ጋብዘዋቸዋል፡፡

## አቶ ታምራት ኪዳነማሪያም - ከኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር (ፕሬዝዳንት)

ጥናታዊ ፅሁፉን ያቀረቡትን አቶ ኃይሉ ቡራዩን፣ ውይይቱን በመምራትና ልምዳቸውን ላካፈሉን ለአቶ ማርሻል ፍቅረማርቆስ እና ለቤቱ በሙሉ ያላቸውን አክብሮት ገልጸው ማኅበሩ የንግድ ኮሚቴ አዋቅሮ ይበልጥ እየሰራ የሚገኝ መሆኑን ገልፀው ምንጊዜም የቤቱ ተሳትፎ እንዳይለያቸው ጠይቀዋል፡፡ ውይይቱ ከቀኑ 7፡00 ሠዓት ተጠናቋል፡፡